# ደንብ

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

**የተያያዙ ርእሶች፡-** ABA, ABA-RA, ABC, ACA, BMA, FAA, IEA, IEB, IED, IFB, IGP-RA, IRB-RA
**ሃላፊ ፅ/ቤት፡-** ዋና የአካዴሚ መኮንን

## የወላጅና የቤተሰብ ተሳትፎ

### I. ኣላማ

ጠንካራ የቤት-ት/ቤት ሽርክና ለማመቻቸት፣ ውጤታማና ሁለገብ የወላጅ/አሳዳጊና የቤተሰብ ተሳታፊነት ልምዶች ለማራመድና ለማሳደግ፣ እና የወላጅ/አሳዳጊና የቤተሰብ ተሳታፊነት የአካባቢ ት/ቤት ማህበረሰቦችን ኣይነተ-ብዙህነት ማንፀባረቁን ለማረጋገጥ ጥረቶችን ለመደገፍ።

### II. መነሽያ ምክንያት

የወላጅ/አሳዳጊና የቤተሰብ በትምህርት ተሳታፊነት በተማሪ ትምህርትና ጤናማ እድገት ኣወንታዊ ውጤት እንዳለው ምርምር ያመለክታል። የግኝት ክፍተትን ለመቀነስ አስፈላጊ ስልት ሲሆን ሰላማዊና በክብረት የተሞላ የመማርያ አካባቢ መኖሩን ለማረጋገጥም ያግዛል።

### III. ፍቺዎች

A. *ማህበረሰብ* በልጆች ትምህርት ላይ ለታለመ ፍላጎት በርካታ የአንድ ኣካባቢ ሰዎችን ያሚያካትት ነው።

B. *ኣይነተ-ብዙህነት* በMontgomery County የትምህርት ቦርድ መመርያ ACA፣ *ፀረ-ኣድልዎ፣ ፍትህ፣ እና ባህላዊ ብቃት* ፍች እንደተሰጠው እውነተኛ ወይም የታሰበ ግላዊ ጠባዮች ላይ የተመሰረቱ፣ ነገር ግን በነዚያ ያልተወሰኑ፣ ልዩነቶችን ያጠቃልላል።

C. የአንድ ልጅ *የቤተሰብ ኣባል* ማለት በደም፣ በጉዲፈቻ፣ ወይም በጋብቻ ዘመድ ማለት ነው።

D. *ወላጅ* ባዮሎጂካዊ ወላጅ፣ ጉዲፈቻ ወላጅ፣ አሳዳጊ ወላጅ፣ እንደ ወላጅ ሆኖ/ና እንዲ(ድት)ሰራ ኣጠቃላይ ስልጣን የተሰጠው/ጣት ሞግዚት፣ የተሾመ ተተኪ ወላጅ፣ በባዮሎጂካዊ ወይም ጉዲፈቻ ወላጅ ፈንታ የሚያገለግል ወላጅ (ኣያትን፣ የእንጀራ-ኣባት/እናት፣ ወይም ሌላ ዘመድን ጨምሮ) ከተማሪው/ዋ ጋር ኣብሮ/ራ የሚ(ምት)ኖር፣ ወይም ለተማሪው/ዋ ደህንነት ህጋዊ ሃላፊነት ያለው/ያላት ግለሰብ ነው/ናት።

E. *የወላጅ ተስትፎ/ግሊቃገብነት* የተመሰረተው፣ ነገር ግን በዚህ ሳይወሰን፣ በብሄራዊ የቤተሰብ-ት/ቤት ሽርክናዎች መመዘኛዎች ላይ ነው።

1. ሁሉንም ቤተሰቦች ወደ ት/ቤት ማህበረሰብ ውስጥ መጋበዝ/መቀበል
2. በውጤታማነት መገናኘት
3. የተማሪን ስኬት መደገፍ

4. ስለልጆች ቆሞ መናገር

5. የመጋራት ሃይል

6. ከማህበረሰብ ጋር መተባበር

## IV. ለአካባቢ ት/ቤቶች ሂደቶች

ሰራተኞች የተከበረ፣ የሚያካትት የት/ቤት ማህበረሰቦች የመገንባት ግዴታ መግባትን እንዲያንጸባርቁ እና ስለ ባህላዊ ብቃትና ውጤታማ የወላጅ/አሳዳጊ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ሙያዊ የእድገት እድሎችን እንዲጠቀሙባቸው ይጠበቅባቸዋል። ጠንካራ የቤተሰብ-ት/ቤት ሽርክናዎች ለመገንባት፣ የአካባቢ ት/ቤቶች የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

A. ሰራተኛ የቤተሰብ-ት/ቤት ሽርክናዎች ብሄራዊ መመዘኛዎችን እንዲገነዘቡ እና መመዘኛዎቹን ለመተግበር ስልቶች መቀበላቸዉን ማረጋገጥ።

B. የወላጅ/አሳዳጊ እና የቤተሰብ ተሳትፎ የሚያራምዱ መገልገያዎችንና ድጋፎችን በመለየትና በመጠቀም ከማእከላዊ ፅ/ቤቶች ጋር ተባብሮ መስራት።

C. ሁሉም ወላጆች/አሳዳጊዎች መልካም አቀባበል እንዲሰማቸውና በክብር እንዲያዙ የሚችሉባቸው ህንፃዎቻቸው ውስጥ አወንታዊ አካባቢ መኖሩን ማረጋገጥ።

D. ወላጆች/አሳዳጊዎች ከቤት እና በት/ቤት በጎ-ፈቃደኛ እንዲሆኑ የተለያዩ እድሎችን ማቅረብ።

E. መልእክተ-ዜናዎች፣ የት/ቤቱ ድርጣብያ፣ listservs፣ myMCPS Parent Portal፣ እና Connect-EDን በሚያካትት፣ ነገር ግን በነዚህ ያልተወሰነ፣ ውጤታማና ወቅታዊ መገናኛ ለማረጋገጥ በበርካታ ዘዴዎችና ቋንቋዎች መገልገል።

F. እንደ Family Math and Literacy nights/የቤተሰብ ሂሳብና መሰረተትምህርት ምሽቶች፣ የትምህርቱን ፕሮግራም የሚገልፁ ዎርክሾፖች፣ ስለ ት/ቤት ሂደቶች መረጃዎች፣ እና የት/ቤትና የማህበረሰብ መገልገያዎች ከመሳሰሉ ግኝትን ለማሻሻል በግልፅ የተገናኙ ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች ለቤተሰቦች ማቅረብ። ት/ቤቶች በት/ቤት ውስጥ ወላጆች/አሳዳጊዎች ቁሳቁሶችን ሊደርሱባቸው የሚችሉበት መስክ ወይም ቦታ መለየት አለባቸው።

G. ወላጆች/አሳዳጊዎችን እንደ የልጆቻቸው ጠበቆች እና እንደ በት/ቤት መሻሻል ሂደት ተሳታፊዎች ለመደገፍና ለመያያዝ ከParent Teacher Student Association/ወላጅ መምህር ተማሪ ማህበር (PTSA) እና ከሌሎች የወላጅ/አሳዳጊ ቡድኖች ጋር ተባብሮ መስራት።

H. በት/ቤታቸው የማሻሻያ ቡድኖች የአካባቢውን ት/ቤት ማህበረሰብ አይነት-ብዙህነት የሚያንፀባርቁ እና በቡድኑ ትርጉም ባለው ሁኔታ ለመሳተፍ እድሉ የሚሰጣቸው ወላጅ/አሳዳጊዎችን ማካተት።

I. ከወላጆች/አሳዳጊዎች አስተያየት ለመሰብሰብ፣ እናም አስተያየቱን ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ለመጋራት፣ Survey of School Environment/የት/ቤት አካባቢ ቅኝትን ጨምሮ፣ ነገር ግን በሱ ሳይወሰኑ፣ በበርካታ ዘዴዎች መጠቀም። በት/ቤት ማሻሻያ እቅድ አግባብ ያላቸው የትግባሬ እርምጃዎች መካተት አለባቸው።

J. የወላጆችን/አሳዳጊዎችን ቅሬታዎች ለመስማትና ለመፍታት የጠራ ሂደት መኖሩን ማረጋገጥ።

K. የተማሪን ትምህርትና የወላጅ/አሳዳጊን ተሳትፎን ለመደገፍ ከአካባቢ ቢዝነስ እና የማህበረሰብ ቡድኖች ጋር ሽርክናዎችን ማዳበር።

## V. የማእከላዊ ፅ/ቤቶች ሂደቶች

በሁሉም ማእከላዊ ፅ/ቤቶች የሚገኙ ሰራተኞች ለወላጆች/አሳዳጊዎችና ለቤተሰብ ተሳትፎ ግዴታ እንዲያሳዩ እና ወላጆችን/አሳዳጊዎችን በሁሉም ግንኙነቶች በክብር የተሞላ ጠባይ እንዲይዙ ይጠበቅባቸዋል። በባህላዊ ብቃት እና በውጤታማ የወላጅ/አሳዳጊና የቤተሰብ ተሳትፎ ሰራተኞች በሙያዊ እድገት እድሎች ይጠቀማሉ። ኣግባብ ያለው/ላት የማእከላዊ ፅ/ቤት ሰራተኛ ት/ቤቶችን በወላጅ/አሳዳጊ የተሳትፎ ጥረቶቻቸው ይደግፋቸዋል/ትደግፋቸዋለች የሚከተሉትንም ይፈፅማል/ትፈጽማለች፡-

A. ለውጤታማ የወላጅ/አሳዳጊና የቤተሰብ ተሳትፎ ስለ ብሄራዊ መመዘኛዎች ለቤተሰብ-ት/ቤት ሽርክናዎች ስልጠና መስጠት እና ከሁሉም የላቁ ልምዶችን፣ ስልቶች፣ እና መገልገያዎችን መጋራት።

B. የወላጅ/አሳዳጊና የቤተሰብ ተሳትፎ ልምዶች በአካዴሚያዊ ፕሮግራሞቻቸው መካተታቸውን ለመደገፍ መምህሮቻቸውንና አስተዳዳሪዎቻቸውን ከሚያዘጋጁ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ጋር መስራት።

C. በት/ቤት መሻሻል ሂደት ወላጅ/አሳዳጊዎችን ለማካተት እና ከብሄራዊ መመዘኛዎች ለቤተሰብ-ት/ቤት ሽርክናዎች ጋር የተዛመዱ የትግባሬ እርምጃዎች ለማዳበርና ለመተግበር ት/ቤቶችን ማገዝ።

D. በmyMCPS Parent Portal፣ Connect-ED፣ የድር ማተሚያ ስርኣት፣ በLanguage Line፣ እና የፁፍና የቃል ትርጉም ኣገልግሎቶችን በሚያካትት፣ ነገር ግን በነዚህ በማይወሰን፣ ባለ-ሁለት ኣቅጣጫ መገናኛቸው ት/ቤቶችን ለማገዝ ተገቢ መሳርያዎች፣ ስልጠና፣ እና ድጋፍ መስጠት።

E. ስርኣት-ኣቀፍ መሻሺያዎች ያስፈልጉ እንደሆነ ለመወሰን እና ት/ቤቶችን በመገናኛ ጥረቶቻቸው ለማገዝ ድጋፎችን ለመለየት፣ የወላጅ/እሳዳጊ ተሳትፎን፣ የት/ቤት ኣካባቢ ቅኝት ጥናት ውጤቶችን፣ እንዲሁም የmyMCPS Parent Portal ቅስቀሳ እና የConnect-ED ኣጠቃቀም ኣሃዞችን በየወቅቱ መገምገም።

F. ስርኣት-ኣቀፍ የወላጅ/አሳዳጊ ቁሳቁሶችን በበርካታ ቅርፀቶች (ህትመት፣ ቪድዮ፣ ድር) እና በበርካታ ቋንቋዎች ማቅረብ።

G. በማህበረሰብ ውስጥ እና በመንግስት ድርጅቶች ኣማካይነት ቤተሰቦች ሊያገኟቸው ስለሚችሏቸው መገልገያዎች ት/ቤቶችን ማሳወቅ።

H. ለት/ቤት የበጎ-ፈቃደኛ ኣስተባባሪዎች መግቢያ/መተዋወቂያና ስልጠና መስጠት እና መላጅ/አሳዳጊዎችን እንደ በጎ-ፈቃደኞች ለማካተት የት/ቤቶች ጥረቶችን መደገፍ።

I. የወላጅ/አሳዳጊዎችን እውቀትና ግንዛቤ ስለ ት/ቤት ስርኣት እና ስለ ኣመርራርና ጥብቅና ክሂሎቶቻቸው እድገት ለማገዝ፣ ስርኣት-ኣቀፍ ፕሮግራሞች፣ ዎርክሾፖች፣ እና ድጋፎች መስጠት።

J. ወላጅ/አሳዳጊዎች በትምህርት ቦርድ በስልታዊ ፕላን ዝግጅት እና የበጀት ሂደት እንዲሳተፉ እና በስርኣት-ኣቀፍ የስራ ቡድኖችና ኣማካሪ ኮሚቴዎች እንዲሳተፉ እድሎች መስጠት።

***የደንብ ታሪክ፡-*** ኣዲስ ደንብ፣ ኦገስት 21፣ 1991፣ ጁላይ 21፣ 2003 ተከለሰ፣ ሴፕተምበር 3፣ 2010 ተከለሰ፣ የተወሰኑ ክለሳዎች ጁላይ 24፣ 2017።